## ሕማማትና በገና እና ሌሎች አጫጭር ታሪኮች

**አጭር ዳሰሳ**

ደራሲ፡- አዳም ረታ
የህትመት ዘመን፡- 2004 ዓ. ም.
የገፅ ብዛት፡- 240
አቅራቢ፡- ቴዎድሮስ አጥላው

**መነሻ**

ይህ የአጭር ልቦለዶች ስብስብ አዳም ለህትመት ያበቃው ሰባተኛ መጽሐፉ፣ ስድስተኛ የአጭር ልቦለዶች መድበሉ ነው። ከ2001 ዓ. ም. ጀምሮ በተከታታይ ዓመታት ከታተሙት መድበሎች ደግሞ አራተኛው እና የመጨረሻው ነው።

መድበሉ አስራ ሦስት የተለያዩ አጫጭር ልቦለዶችን ይዟል። እነዚህ ተረኮች በአተራረክ ስልታቸው፣ ወይም በገጸባሕርያቶቻቸው ሐሳብ/ ስሜት/ ባህርይ፣ ወይም በቋንቋቸው፣ ወይም በሌላ በሌላ ነገሮቻቸው ቀድመዋቸው የታተሙትን ሌሎች የአዳም ተረኮች ያስታውሱናል። ይህኛው መድበል እንደቀድሞዎቹ ሁሉ የአዳምን የመረጠውን ረቂቅም ይሁን ግዙፍ ነገር አንጀት በሚደርስ ቋንቋ የመግለፅ ብቃት የታየበት ነው። አብዛኞቹ ተራኪዎች ስሜታቸውን እና ሐሳባቸውን በገለጻቸው ያጋቡብን እና ስለአጭር ልቦለድ ባህርያት ከስነጽሑፍ መምህራን የሰማነውን/ ያነበብነውን ደንብ አስረስተው፣ ከተለምዷዊው የስነጽሑፍ እውቀት ራቅ ብለን እንድናስብ ያደርጉናል።

በዚህ ንግግር ሁሉን መተንተን ስለማይቻል በተወሰኑ ነጥቦች ላይ በማተኮር እኔ ይህን ሕማማትና በገና የተሰኘ መጽሐፍ እንዴት እንደተረዳሁት ለማሳየት እሞክራለሁ።

### 1. የተለዩ የአተራረክ ስልቶች

መድበሉ ከአዳም ሥራዎችም ይሁን ከሌሎች የአማርኛ ድርሰቶች የተለዩ ቴክኒኮች የታዩባቸው ሁለት ድርሰቶችን ይዟል።

**ሀ. "የሐር ነዶ"**

በአዳም ድርሰቶች ውስጥ የደራሲው መለያ እስኪመስለን ድረስ ከትረካዎች ይልቅ ገለፃዎች ገዝፈውም በዝተውም ይሰሙናል። ይህ አጭር ልቦለዱ ግን ይለያል። ምንም ገለፃ፣ ምንም ትረካ፣ ምንም መግለጫ የለውም። ተተረከ ከተባለ የሚተረከው በሦስት ገጸባሕርያት ምልልስ እና በመቼት ጥቆማው ብቻ ነው። ድርሰቱ ውስጥ ያሉትን አባት፣ ልጅ እና የልጅን ጓደኛ የምናውቃቸው፣ ይህንን ግንኙነታቸውን እንኳን የምናውቀው ነጋሪ ተራኪ ኖሮን አይደለም። ምንትነታቸውን፣ ድርጊታቸውን፣ ሴራቸውን፣ ወዘተ በሚለዋወጡት ቃላት አማካይነት ብቻ ነው የምንገነባው።

እንደ ልማዱ ከንግግሮቻቸው በኋላ ንግግሩ የማን እንደሆነ አይነገረንም፣ ከሒደቱ እንድንረዳው ይደረጋል እንጂ። የዳንሱን፣ የጸጉር መሠራቱን፣ የመሽሞንሞኑን፣ የመሽኮራመሙን ነት ድርጊቶች ሳይቀር የድርሰቱ ምሰሶም ማገርም ከሆነው ከምልልሱ ብቻ ነው የምንረዳው። ከተውኔት እና ከፊልም ድርሰቶች እንኳን በእጅጉ ያነሰው የመቼት ጥቆማ እንደ ጥሪ ካርድ ቦታ እና ሰዓቱን ብቻ ነው የሚነግረን።

ምንም እንኳን በሺ ገፅ የተጻፈም ድርሰት ቢሆን ያለ አንባቢው ተሣትፎ ሙሉ እንደማይሆን ቢነገርም (አንዳንድ ሐያሲዎች "the meaning of a literary work has no effective existence outside of its realization in the mind of a reader" እንዲሉ)፣ ይህ በምልልሳዊ ስልት የቀረበው "የሐር ነዶ" ግን እንዲያውም አብዛኛውን የድርሰት አጻጻፍ ልማድ የሰጠውን *ኃላፊነት* ለአንባቢው የተወ ድርሰት ነው።

## ለ. "ትይዩ"

አንድ ፈረንጅ አገር ያለ ሐበሻ እና አንዲት ነጭ የሆነ መጠጥ ቤት ሩቅ ለሩቅ ተቀምጠው የመፈላለግ ጨዋታ በዓይኖቻቸው ሲጫወቱ የሚያስቡትን እና የተሰማቸውን ጎን ለጎን የሚያሳይ ድርሰት ነው። ድርሰቱ ያረፈባቸው የመጽሐፉ ገፆች በሁለት አምድ ተከፍለው የአንዳቸው ሐሳብ እና ስሜት በነጭ መደብ ላይ በጥቁር ፊደላት፣ የአንዳቸው ደግሞ በጥቁር መደብ ላይ በነጭ ፊደላት በትይዩ ቀርበዋል።

ሁለቱም በተመሳሳይ ሰከንድ ምን እንደሚያስቡ፣ ምን እንደሚያደርጉ፣ ምን እንደሚደረግባቸው ሁሉን አወቁ ተራኪ አንዴ ወደ እሱ፣ አንዴ ወደ እሷ እያመላለሰ፣ እሱ ሳይተርክ እነሱን ያናዝዝልናል። አንድ ተረክ ከአራት ዓይኖች እና ከሁለት ልቦች አንጻር እናነባለን። በወንድ እና በሴት ዓይኖች እና ልቦች። ያውም የባህል ርቀት ባለባቸው፣ ፋከራና ሽለላ በሚነሽጠው የሐበሻ ወንድ እና "ከኋላ መደረግ ትወዳለች" ተብላ በምትታማ "ሉዘር" ነጭ ሴት ዓይኖች እና ልቦች።

"ትይዩ" እንደስሙ የሁለቱን ተፈላላጊዎች ልብ በትይዩ ያሳያል። አንዳንድ ጊዜ ትረካዎች ከአንድ ገፀባህርይ አንጻር ሲተረኩልን፣ ትረካው ውሱን እንደመሆኑ መጠን፣ የተነገረን በቃን ካላልን በቀር የትረካውን ጎደሎ እኛው ነን ከባህል፣ ከአብሯደጎቻችን፣ ከትምህርት፣ ከሌላም ከሌላም በቀዳነው እና አጣርተን ባከማቸነው ግንዛቤ አማካይነት የምንሞላው። ጉዳዩን ጠበብ እናድርገው እና ስለቴዲ ከጓደኛው የሰማነውን ወሬ ከራሱ ከቴዲ እንስማው ብንል በልቦለድ ውም በአጭር ልቦለድ ውስጥ ያንን ዕድል አናገኝም። ይህንን በዚሁ መድበል ውስጥ ባሉ ተረኮች ምሳሌነት እንየው፡-

"ቀጠሮ እና እሷ" — "ትራፊ ነው የሚደርሰኝ" የሚል፣ በፍቅረኛው ቀጠሮ አለማክበር የተማረረ ገፀባህርይ ነው ምሬቱንም፣ ንቀቷንም፣ ፋከራውንም፣ ውስልትናዋንም የሚነግረን። እንደተጫወተችበት ሲነግረን እና አሁን ስትመጣ እንዴት እንደሚቀጣት እሷን የሚጠብቅበት ቦታ ተቀምጦ ሲደነፋብን ይቆይ እና እሷ ስትመጣ ይልፈሰፈሳል። *ታዲያ* እንደ ተሣታፊ አንባቢነታችን ይሄንን ሰው እንዲህ እየናቀችው ከምታንገላታው፣ ወደተሻሉት ወዳጆቿ እንደሔደች የማትቀርለት ለምንድነው የሚል ጉጉት ሊያድርብን ቢችል ከድርሰቱ መልስ አናገኝም፤ ከየራሳችን መላምት ውጭ።

ለመጽሐፉ ርእስ ያዋሰውን "ሕማማትና በገና" የተባለውንም ዘለግ ያለ ድርሰት ብናይ ከዚህ የባሱ ጥያቄዎች እንደተፈጠሩብን ነው ድርሰቱን አንብበን የምንጨርሰው። የዋናው ገጸባህርይ ጉዳይ ጥያቄ እንደሆነብን እንቀራለን። የጉርምስና ዋዜማ ላይ ያለው ተራኪያችን ቴንሳ፣ ብርሃኑ ማነው፣ ለምንስ ነው ይህን ሁሉ ቀንበር እሺ ብሎ የተሸከመው፣ ለምን አይናገርም፣ ብለን ጥያቄ ብናከታተልበት እሱ ወደ እድሜው ጣጣ ገብቶ ብርሃኑን ሊያረሳሳን ሁሉ ይሞክራል - እንኳንስ ሊመልስልን።

"ትይዩ" ከሌሎቹ ተረኮች አንጻር "ሁለት በአንድ" ዓይነት ድርሰት ነው። የተረኩ ግማሽ ቢጎድል እንደሌሎቹ አንድ ይሆናል፤ ሙሉውም ቢኖር አንድ ነው። በዚህ መድበልም ሆነ በአጠቃላይ የአጭር ልቦለድ አጻጻፍ ልማድ መሠረት፣ የሁለቱ ተራኪዎች ትረካዎች ራስ ራሳቸውን ችለው ሁለት ቢሆኑ፣ ለአንባቢው የቤት ሥራ ሰጥተው ከነተረካዊ ምልዐታቸው ይኖራሉ፤ በትይዩ በመተረካቸው ደግሞ የአንባቢን ጥያቄ መልሰው በሌላ ምልዐት ይኖራሉ።

## 2. ዝምታ ወርቅ አይደለም

ይህ የአጫጭር ልቦለዶች መድበል፣ በርእሰጉዳይነት ወይም በጭብጥነት ደረጃ አንደበት ትልቅ ቦታ ያገኘበት መድበል ነው። ሦስት ተረኮች ላይ የምናገኛቸው ዋነኛ ገጸባህርያት ሐሳባቸውን እና ስሜታቸውን በቃላት የመግለፅ እክል አለባቸው። ሁለቱ በዓይናፋርነት፣ አንዱ ደግሞ በአካላዊ ጉዳት ምክንያት። ሦስቱም ባለመናገራቸው ምክንያት በሚኖሩበት ማኅበረሰብ ጅራፍ የሚዠለጡ ወኪሎቻችን ናቸው።

በድርሰት አደራደር ቅደም ተከተላቸው እንያቸው፡-

### ሀ. የ“ዐይን” ተራኪ

ማውራት አልወድም ይላል። የንግግርን በማይክሮስከንዶች የሚጠናቀቅ ሒደት አዝግሞ የሚያስብ፣ አሠራሩንም ተፀይፎት እኛም እንድንፀየፈው የሚገፋፋን ወጣት ነው። የማውራት ድርጊት ይደክመኛል ይላል፡-

> *ማውራት ስጀምር ከንፈሮቼ ይከብዱኛል...ድምፄን ከጉሮሮዬ እንደዕቃ እንደ ቁምሳጥን፣ እንደ አሎሎ፣ እንደምናምን ገፍቼ ማውጣት አለብኝ። ብዙ ጊዜ አይሆንልኝም። ለምሳሌ አጫጭር ቃላት ቶሎ ቶሎ ሲወጡ ረጃጅሞቹ ሲጎተቱ ሲንቀራፈፉ ይታወቀኛል... ታዲያ ረጃጅሞቹን ለማውጣት እጆቼን አወዛውዛለሁ... ትከሻዎቼን እንደእስክስታ አነቀንቃለሁ። አንዳንዶቹ ቃላቶች አእምሮዬ ጫካ ውስጥ ያለምንም ዱካ አድራሻቸውን ሳይጠቁሙኝ ይጠፋሉ...*
> (ገፅ 93)

የመናገር ሒደት ቀላል ስላልሆነለት ሳይናገር ቢቀር ለተለያዩ ስያሜዎች ተጋልጧል። በዙሪያው ያሉ ሰዎች ኩራተኛ፣ ትዕቢተኛ፣ ጨዋ፣ ድብርታም፣ ፈሪ የሚሉ ስሞችን ለጥፈውበታል። አለመናገሩ አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ቅፅሎችን ቢያስጠውም፣ ሰውየው አንደበቱ በመታሰሩ በደንብ ያያል፣ ያሸታል፣ ያዳምጣል፤ በአጠቃላይ ይመዘግባል። ከአዳም “መዝገቡዎች”ም እንደ አንዱ ሆኗል።

ህይወቱ ከራሱ ጋር በሚያደርጋቸው ጭውውቶች የተሞላ ይመስላል። በተፈጥሮ መናገር ሳይሳነው ለማይናገር አባሉ ማኅበረሰብ ቦታ እንደሚነፍግ ተረድቶ ይሆናል። “...እየዳህኩ፣ እየተበታተንኩ ከጫወታው እየራቅሁ ወደማይሰለቸኝ ዓለም እጠፋለሁ።..” ይለናል (ገፅ 94)። ዝምታን ከሚፈራው ዓለም ሸሽቶ የአንደበት ፈተና ወደማይኖርበት፣ ወደ የምናቡ መስክ መሰስ ብሎ ይገባና እያለ ይሰወራል።

### ለ. ብርሃኑ፣ “ሕማማትና በገና”

ተራኪው ከ“መዝገቡዎቹ” አንዱ የሆነ፣ ቴንሳ ዘነበ ቴንሳ ተባለ ልጅ ነው። ስለብርሃኑ ራሱን እና መንደሩን ወክሎ ይተርክልናል።

ብርሃኑ ተብታባ ነው። ዓይናፋር ነው። ባይተዋር ነው።

ከዓይናፋርነቱ የመነጨ የሚመስለው ተብታባነቱ እና፣ ምናልባትም በዓይናፋርነቱ እና በተብታባነቱ የተባበረ ክንድ የተዘጋው አንደበቱ እንደ ቁል ያስቆጥረዋል። የሙሉ ሰውነት ክብር ያስነፍገዋል። ዝምታው ያስጠቃዋል።

ለምሳሌ ሚስት ሊያገባ ነው የሚባል ወሬ ሲናፈስ፣ ጎረቤቶቹ የእሱ ማግባት ተገቢ እንዳልሆነ፣ እሱ ለትዳር ብቁ እንዳልሆነ ሲናገሩ እንጂ ሲደሰቱለት አንሰማም፤ አናይም። የአንደበቱ መተሣሠር እና ዝምታው ትዳር የሚባለው የማኅበረሰብ ተቋም ውስጥ ለመግባት የማያበቁ ጉድለቶቹ ስለመሆናቸው እንሰማለን።

*" እሱ ያግባ! ስሙን እንኳን አስተካክሎ የማይናገር..."*

*" እሱ እቴ አይናገር አይጋገር..."*

*" ራቴን ስጪኝ ለማለት ወር ሳይወስድበት አይቀርም"*

በዝምታው አክስቱ በቤት ሠራተኛነት ያመጡለትን ሴት ለማግባት ይገደዳል። በዝምታው ምክንያት ይህች ሴት ከጓደኞቹ ነጠለችው፤ ጎረቤቶቹን ነጠቀችው፤ እንደ ሰው የሚያየውን እንደ ልጅም እንደጓደኛም የሚወደውን ፍየሉን አሳርዳ አበላችው ( ወይስ እርም ነው ብሎ ተወላትና በላችበት?) ፤ ቆዳውን በገና አድርጎ በገናውን የሕማማቱ ጊዜው ወዳጁ ቢያደርግ እሱንም ያለፈቃዱ ወስዳ ከፈረንጅ ተወዳጀችበት። የእኔ የሚለውን አሣጥታ፣ ያንተ ነው ያለችውን ልጅ ልታሳቅፈው ወደደች፤ ያንተ ናት ተብላ የተሰጠችው ይህቺ ስሟ እንኳን የማይያዝለት ሚስቱ እሴቶቹን ሁሉ ነጥቃ፣ በዝምታው ያጠረውን የነጻነት ቅጥሩን አፈራርሳ እርቃኑን አስቀረችው።

በእርግጥም ማኅበረሰብ ውሸቱን ነው። ዝምታ ወርቅ አይደለም። ማኅበረሰብ ዝምታን እና ዝምተኞችን እንዳደባ አውሬ ይፈራቸዋል። ዝምታ ጨለማ ነው። ጨለማ ደግሞ ውስጡ ምን እንደያዘ ቢታወቅም ስለሚያጠራጥር ያስፈራል፤ ዝምታም ለማኅበረሰብ እንደጨለማ ውስጡ ምን እንዳለው የማያሳይ አስፈሪ ነገር ነው።

ጎረቤቶቹ ብርሃኑን ቂል ነው ብለው የናቁት ይምሰሉ እንጂ፣ ህፃኑ ቴንሳ ከሚፈራው በላይ ይፈሩታል፤ አድብቶ ጊዜ እንደሚጠብቅ አውሬ የሆነ ቀን እንዳያጠፋቸው ይሰጉበታል። ለዚህ ነው የቴንሳ አባት " እንደዚያ አይነት ዘዝም ብሎ የከረመ ሰው የሚያደርገው አይታወቅም" ብሎ ፍርሃቱን ለሚስቱ ሲያጠይቅ የምንሰማው። ይሄው ነው።

**ሐ. ዘገየ - "ርእዮተ ሥጋ"**

ምላስ የሌለው አዝማሪ።

ዋናው ባለታሪክ እና ተራኪው ሰክሮ ምላሱ የተጎዳበት ዘገየ ነው። በአዲስ ዓመት ዋዜማ ሰክሮ ደጃፉ ላይ ወድቆ ምላሱ የተከረተፈበት ዘገየ አዝማሪ ነው። " አዝማሪ ስለሆንኩ ምላሴ እንጀራዬ ነው፣" ቢልም በምላሱ ላይ በደረሰበት አደጋ ምክንያት ለእንጀራው ሊዘፍን ቀርቶ፣ ስጋቱን፣ ብስጭቱን፣ ሐሳቡን መናገር የተሳነው ዲዳ ሆኗል። ለጊዜውም ቢሆን ህልውናው በምላሱ ላይ ተመሥርቶ፣ ቤተሰብ የመሠረተ አዝማሪ ነው።

ደሃው ዘገየ ግጥሙን ከዜማ አስማምቶ፣ በማሲንቆ እያጀበ ታዳሚውን በአንደበት ኪነቱ ሲያዝናና ሊያመሽ ቀርቶ፣ የጎረቤቱን ፋክክር ከሚገጥመው ነገረኛ፣ ጉረኛ፣ ውሸታም፣ አብሻቂ ትንኮሳ እንኳን መ ቋቋም ይሳነዋል።

መናገር አለመቻል ያንዳንድ ሰው ትራጀዲ ነው። የ" ዐይን" ዓይናፋር ተራኪ መናገር ቢጠላም፣ አያድርስ በሚያስብል ምፀት " ወሬ እወዳለሁ" ይለናል። ወሬ እየወደደ ማውራት ይጠላል። ይኸው ለአዝማሪው ዘገየ ደግሞ ምላስ ማጣት፣ አቅም ማጣት ጭምር ነው፤ መናገር ባለመቻሉ እጁን አወናጭፎ ይቀራል። አለመናገሩ የጎረቤቱ መጫወቻ ያደርገዋል።

### 3. "ሁላችንም አክተሮች ነን"

መድበሉ ትንሽ መንደር ቢሆን፣ የአስመሳዮች መንደር ነው ማለት እንችላለን። ከህጻን እስከ አዋቂ ደግ ቢታሰስ ማግኘት ይከብዳል። አስመሳይ ይበዛዋል። ተንኮለኛ ይበዛዋል። በሴት እና በወንድ ግንኙነት እምነት የሚታጣበት መንደር ነው። ህይወትን እንደመድረክ የሚያይ፣ የኑሮ ድርሻውንም እንደተወና የሚወጣው ኗሪ/ ተዋናይ ሙብዛቱ።

**እዩት፦ ደሣለኝን፣ "ስንዝሮ" ውስጥ አመድ በዱቄት ሲለውጥ፣**

ወትሮም በቤተሰቦቻቸው የቃል ኪዳን ካቴና የታሰሩት ጥንቅሽ እና ዓቢይ፣ በዓቢይ ጓደኛ መሣይ በደሣለኝ ሴራ ተለያይተው ይቀራሉ። ዓቢይ የሚወዳትን እና ወላጆቹ የሰጡትን ጥንቅሽን አምኖ ምስጢሩን ባካፈለው በጓደኛው ይነጠቃል። ይህ እስኪለይለት ድረስ ግን በአስመሳዩ ደሳለኝ ሽርክና የዓቢይ ገንዘብ በጥንቅሽ የማስመሰል ጥበብ አማካይነት ይበዘበዛል።

ደሣለኝ ቆንጆዋን ጥንቅሽን ከቤቷ ወስዶ፣ ከቡና ቤት ያገኛትን ወለላን ለዓቢይ በልዋጭነት ይሰጠዋል፤ ዓቢይን " ሲያወጡ ከቡና ቤት፣ ሲያገቡ ከቡና ቤት" ለሚል የማኅበረሰብ አለንጋ አሣልፎም ይሰጠዋል። ደሣለኝ ስንዝሮ ነው፤ በተረት አመድ በዱቄት ስለመለወጡ የሰማንለትን የብልጣብልጡን ስንዝሮን ምግባር ይጋራል። በነገራችን ላይ፣ ይህኛው ስንዝሯችን ከዓቢይ ጋር ስለተገናኙበት፣ ጓደኝነታቸው ስለተጠነሰሰበት፣ ወለላም ስለተገኘችበት ቡና ቤት የሚነግረን እንደመፈላሰፍ እያደረገው ነው፤ ተራኪያችንም እሱው ስለሆነ ከዚህ ቀጥሎ የምነግራችሁ ታሪክ እንዳይደንቃችሁ፣ ዓለም እንዲህ ናት ብሎ ያመቻቸናል፦

> *ቡናቤት አሉት እንጂ ቦታው መድረክ ነው። እዛ የሚመጡት ሁሉ ተዋንያንና ደራሲዎች ናቸው። ሁሉም የራሱን ድርሰት እየጻፈ ይመጣና ይተውናል።* ( ገፅ 19)

እንግዲህ ደሣለኝ አዛኝ፣ አሳቢ ጓደኛ መስሎ ረቂቅ ሴራ ያለውን ድርሰቱን ጽፎ መተወን የጀመረው እዚሁ ቡና ቤት ውስጥ ነው።

**እዩዋቸው ደግሞ አባት እና ልጅን፣ ሶፊንም ጭምር - "የሐር ነዶ" ውስጥ**

የተወሳሰበ ሴራ። ልጅት ምንም እንደማታውቅ ሆና ሽማግሌ አባቷን ከጓደኛዋ ከሶፊ ጋር ታወዳጃለች፤ አባት ልጁ የማታውቅ እያስመሰለ የልጁን ጓደኛ ያበስላል፤ ሶፊያ ጓደኛዋን የሸወደች እየመሰላት እና አባቷንም " የምትፈራቸው" እያስመሰለች ከጓደኛዋ አባት ጋር ትወጣለች። ሶፊ " ሁላችንም አክተሮች ነን" የሚል ፍልስፍናዋን እያጠጣችን፣ እየተሸወደች ትሸውዳለች።

አባት እና ልጅ ተማክረው ሶፊን ቢያታልሏትም፣ እሷም ያታለለች ስለሚመስላት እና አባትየው ስለሚወዳት አትጎዳም። ሆኖም ግን ሁሉም ኑሯቸውን ከማስመሰል የገነቡ ሐሳዊያን ናቸው።

**እዩዋቸው መምህራኑን፣**

" *የምሥራች! ልጅ እንደ እናቷ ሆነች*" ውስጥ፣ ትናንሾቹን እነኤሊያስን ትምህርት ቤት ውስጥ አርቤሽት ተጫወታችሁ ብሎ ምግባር ሊያስተምራቸው የሚዳዳው የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር፣ ሌላዋን ተማሪ በወሲብ ለውጥ ፈተና ያሳልፋታል፤ ሌላውን ደግሞ በትእዛዝ ያሳልፋል። መምህሩ ሥልጣኑን ተጠቅሞ አንዲት ፍሬ ልጅ ያባልጋል።

" *መስከረምና መስከረም*" ውስጥ ደግሞ የስፖርት መምህሩ እንግዳ ለተማሪዎቹ " ስለ ስነስርዓት እና ስለ ባሕል" መስበክ የሚቃጣው አዋቂ ነኝ ባይ መምህር ነው። ነገር ግን እሱም ይቺኑ የመምህርነት ሥልጣኑን ተመክቶ ተማሪውን የወሲብ ፍላጎቱ ማርኪያ ለማድረግ ጥረት ሲያደርግ ይታያል።

እንዲያው ትእግሥት ኖሮን እዚህ መድበል ውስጥ ያሉትን በቃላት አጥንት እና ሥጋ ተሰጥቷቸው፣ በንባባችን ነፍስ የምንዘራባቸውን ገፀባህርያት በሙሉ ብንመረምራቸው፣ አንዱ ቂል ገጸባህርይ እንዳለው፣ በትንሳዔ ጊዜ “በእግዜር ግራ” የሚሰለፉ ናቸው። በተጨማሪ ምሳሌነት ካሲ (ከይሲ)፣ ወ/ሮ ደብሪቱ፣ ሳባ እና ዘሴ ሊጠቀሱ ይችላሉ።

**በመጨረሻም፣**

ይህን መድበል ደጋግሜ ሳነብ ያየኋቸው እና መጽሐፉ ለድጋሚ ህትመት ከገባ ከግምት ሊገቡ የሚገባቸው ጥቃቅን መሳይ ስህተቶች አሉ። ለምሳሌ

- “ዐይን” ውስጥ ስለ አንድ ልጅ “የጋሼ የእንጀራ ልጅ …” እና “ከመጀመሪያ ሚስቱ የወለደው” የሚሉ መግለጫዎችን እናገኛለን፤
- “ሕማማትና በገና” ውስጥ፡- “የዓመቱ ተዝካር እንደወጣ፣ አስገዶም የሚባል ሰው ከከተማ ሊጠይቃት መጣ ተባለና አብሯት ከረመ። ብርሃኑ ከሞተ ዓመት ሳይሞላው ከአስገዶም ጋር ተጋብተው ሁለተኛ አርግዛ አየሁአት።” (ገፅ 166) የሁለቱን ያሰመርኩባቸውን የጊዜ መግለጫ ሐረጎች ልዩነት ልብ ይበሉልኝ።
  እዚሁ ተረክ ውስጥ ተራኪያችን ቴንሳ፣ “በአባቴ አያት ስም ነው የምጠራው፣” (ገፅ 131) ቢለንም፤ ስሙ ግን ቴንሳ ዘነበ ቴንሳ ነው። የቴንሳ ዘመዶች አባቶች ለልጆቻቸው የራሳቸውን ስም የሚሰጡበት እንደማይሆን እገምታለሁ።
- “ርእዮተ ስጋ” ውስጥ፡- ባለማሲንቆው አዝማሪ፣ ማሲንቆውን ስለመጠገን እየነገረን፣ “በመደበሬ ክራሬን የመጠገን ስሜቴ” ይላል (ገፅ 211)።
- በተደጋጋሚ ያጋጠሙኝ ስህተቶች የግዕዝና እና የአማርኛ ብዜት የተደረቡባቸው ቃላት ናቸው። በግዕዝ ድርብ ድርብርብ ብዜት እንዳለ ብሰማም፣ ያ ግን የሁለቱን ቋንቋዎች የማብዛት ስልት ደባልቆ ድርብርብ ብዜትን መፍጠርን የሚያካትት እንደማይሆን አምናለሁ። ምሳሌ፡- በቃላት ወይም በቃሎች ፋንታ “ቃላቶች”፣ በወራት ወይም በወሮች ፋንታ “ወራቶች” የሚሉ ቃላትን አዘውትሮ የመጠቀም ነገር አይቻለሁ።